# ሆርሞን (Hormones)

ሆርሞን (Hormones) በሰውነት ውስጥ የሚገኝ የተፈጥሮ ንጥረ ፈሳሽ ነው። ደም ይህንን ሆርሞን (Hormones) ተሸክሞ በሰውነት ውስጥ በመንቀሳቀስ ለተለዮ ሕዋሳት ያቀብላል። ሰውነታችን የተገነባው ከነዚህ በሚሊዮን ከሚቆጠሩ ጥቃቅን ሕዋሳት ነው። እነዚህም የቆዳ ሕዋሳት፣ የጡንቻ ሕዋሳት የደም ሕዋሳትና ሌሎች ብዙዎችን ያጠቃልላል። ለዚያ የተለየ ሆርሞን ተቀባይ የሆኑ የተለዩ ሕዋሳት ሬሴፕተርስ (Receptors) ይባላሉ። ሆርሞንና ሆርሞን ሬሴፕተርስ በአንድ ላይ እንደ ጉጓንችርና ቁልፍ አብረው ተደጋግፈው የሚሰሩ ናቸው። ማለትም ቁልፍ ጓጉንቸሩ ላይ ካልገጠመና የራሱ ካልሆነ በሩን ሊከፍት አይችልም። ስለዚህም ሆርሞኑ ከሬስፕተሩ ጋር የሚገጥም ከሆነ ሕዋሱ ላይ ውጤቱን ያሳያል ማለት አለበለዚያ የማይጣጣምና የማይገጥሙ ከሆነ በሕዋሱ ላይ ምንም ለውጥ ወይም ውጤት አይኖርም።

የሴት ጡት ሕዋሳት ኤስትሮጂንና ፕርሮጂስትሮን የሚባሉ ተቀባዮች (Receptors) አሏቸው። እነዚህም ተቀባዮች በሆርሞኖቹ የሚላከውን መልክት ተቀብለው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይመለከታሉ። ስለዚህ እነዚህ ሆርሞኖች ለተቀባዩ (Receptors) የጡት ሴሎች እንዲያድጉ በር መክፈት ከሆነ ይከፍታሉ ወይም የስሜት ፍላጎት (Stimulate) እንዲሁ ያደርጋሉ። የጡት ካንሰር ሴሎችም እንደዚሁ ተቀባይ አላቸው። ኤስትሮጂንና ፕሮጂስትሮን (Estrogens and Progestone) በአግባብና ያለአግባብ ያሉትን የጡት ሕዋሳት እንዲባዙ ያደርጋል።

ሐኪምዎ የሆርሞን ተቀባይ ሙከራ ምርመራ እንዲደረግ ያዛል። ይህም የሙከራ ምርመራ የካንሰሩ ሕዋሳት የሆርሞን ሬሴፕተር (Hormones Receptors) እንዳለው ያሳያል። የካንሰሩ ሴሎች ለሆርሞን ፕሮጄትሮን (Hormone Progestone) ተቀባይ (Receptors) ካላቸው ፒአር-ካንሰር-ገብ (PR-positive) ተብሎ ይጠራል። የጡት ካንሰር ሕዋሳት ለዚያ ሆርሞን ተቀባይ የሌላቸው ካንሰር-አልባ (PR-positive) እንደሆነ ያሳያል። ኢ.ር -ካንሰር-አልባ (negative) እና ፒአር-ካንሰር-አልባ (ER-negative) ለሆርሞን ቴራፒ (PR-negative) ምንም ምላሽ አይሰጡም።

ሆርሞን ሬሴፕተርስ ያላቸው ኢ.አር-ካንሰር-ገብ (ER-positive) እና ፒአር-ካንሰር-ገብ (PR-positive) የጡት ካንሰር ዓይነቶች ለሆርሞን ቴራፒ (Hormone therapy) በደንብ አድርገው ምላሽ ይሰጣሉ። የሆርሞን ቴራፒ በሚሰጥበት ጊዜ አንዳንድ የሚሰጡት መድሐኒቶች በሰውነት ውስጥ ያለውን የሆርሞን መጠን ሲቀንስ ሌሎች መድሐኒቶች ደግሞ ሆርሞኖቹን ከተቀባዩ (Receptors) እንዲርቁ ያደርጋሉ። ይህም የካንሰሩን ሕዋሳት እንዳያድጉ ወይም እንዳይባዙ ለመግታት ይረዳል። ታሞክሲፌን / ኖልባዴክስ (Tamoxifen Nolvadex) የሚባለው መድሐኒት ኤስትሮጂን ሆርሞን ተቀባይ ለሆነው ወደጡት ካንሰር ሕዋሳት እንዳይደርስ ያቆመዋል። ካንሰሩ ሆርሞን ተቀባይ ባይኖረውም ሌላ በጣም ፍቱን የሆነ የማከሚያ ዘዴዎች አሉ።